



ቅፅ ፩ ቁጥር ፪ መስከረምና ጥቅምት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. VOLUME 1, ISSUE 2 OCTOBER 2005




**የአንድ ቀን መዘዝ ያለዘጠኝ ወር አይመዘዝ**

*ዘነበች ከሲያትል*




## ይህ ቀን አልፎ አድዋን ድል አድርገን አዲስ አበባ እንገባ ይሆን?

*ከተክለሚካኤል አበበ*



"... ይህ ኢህአዴግ የያዘው አቅጣጫ ለሀገራችን፡ ለኢህአዴጎች ለራሳቸውም የማይበጃቸው መሆኑን ውጭም ያለው ውስጥም ያለው በሰላማዊ መንገድ ኢህአዴግን በአፅንኦት ማሳሰብ ያስፈልጋል ..."

*ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማሪያም*

**እኛና እህል**

*ያሬድ ክንፈ ከስዊድን*

# ማለዳ

ማለዳ ቅፅ ፩ ቁጥር ፪
MALEDA VOLUME 1, ISSUE 2
መስከረምና ጥቅምት
፲፱፻፺፰ ዓ.ም.
OCTOBER 2005

## ቃለምልልስ



"... አሁን ህዝባችን ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሷል፣ ከዳር እስከዳር ይህን ምርጫ ይህ መንግስት አጭበርብሮ ነው ያሸነፈው፣ ተሰውቼ፣ ታግዬ ያገኘሁትን ድል ተቀምቻለሁ የሚል በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ነው ...
"ምርጫ የድል አጥቢያ አርበኛ ነው"
ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

"... ደህና ይህ ስም ማጥፋት እኮ ትግል ማጥፋት ማለት ነው። ከእኛ ልምድ በስም ማጥፋት ይጀመርና አቋምን ማንቋሸሽ፣ በሰው ላይ በግለሰብ ላይ ማተኮር፣ ... ይሄ የኢህአዴግ ታክቲክ (አካሄድ) ነው። እናም ትግልን ማጥፋት ነው እንጂ ምንም ልማት የሚያመጣ ነገር አይደለም። ስለዚህ አንደኛ ነገር፣ እንደዚህ የሚሰነዝሩ ሰዎች በግድ መቀጣብ አለባቸው። በተለይ አሁን ባለንበት ደረጃ። ሁለተኛ ነገር ደግሞ ስማቸው ይጠፋል የተባሉ ሰዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ንቀው መተው ነው ያለባቸው። አሁን ከምርጫው ወዲህ በግለሰብ ደረጃ እንደኔ የሚወረድበት ያለ ሰው አይመስለኝም። በኢህአዴግ በኩል በተቃዋሚ በኩል ሳይሆን በኢህአዴግ በኩል። ማን ዝም ብዬ ነው የምተወው። ..." ... **በገፅ ፯**

→ p6

## ዛሬ



"... በተጨማሪ ደግሞ መንግሥት ራሱ ሕገ-መንግሥቱን ጥሷል። መንግሥት ሕገ-መንግሥቱን በሚጥስበት ጊዜ ለህዝቡ ምን አይነት ምሳሌ ነው የሚሆነው? ህዝቡን ራሱ "ሕገ-ወጥ ሁን፣ ሕግ አልባ ሁን" ማለት ነው። ስለዚህ የተለያየ የሕገ-መንግሥቱ አንቀፆች እንደተጣሱ የሚያጠራጥር ነገር አይደለም። ..."
ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማሪያም ... **በገፅ ፱**

## ጥበብ

" ... የምወደውን ነገር በሙሉ አጥቼ ነው የመጣሁት። ... እንግዲህ ደስታ በምን ይለካል ነው? ደስታ በምትነዳው መኪና፣ በምታገኘው ገንዘብ ልክ፣ በምትኖርበት ቤት ጽዳት አይደለም የሚለካው። ደስታ አይለካም አይገዛም። ያን ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረኝን ደስታ አላገኘውም ...

አርቲስት ታማኝ በየነ **በገፅ ፲፭**



## ግልገል ማውጫ

| | |
|---|---|
| መልዕክቶቻችሁ | ፪ |
| የማለዳ መልዕክት | ፫ |
| ሐገር እንዴት ሰነበተች | ፬ |
| ቃለምልልስ | ፯ |
| ዛሬ | ፱ |
| የማለዳ ስንቅ | ፲፩ |
| የኛ ሰው በስደት | ፲፫ |
| ጥበብ | ፲፭ |
| ዓለም አቀፍ | ፲፯ |
| የግጥም መድብል | ፳ |
| አጫጭር ዜናዎች | ፳፩ |
| እንተዋወቅ | ፳፪ |
| ሹክ ልበልዎ | ፳፫ |
| ከ/ለ-አገር ቤት | ፳፬ |
| ትዝብት | ፳፯ |

# ቃለምልልስ

በአትክልት መሸሻ



**በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ከፍተኛውን ሚና በመጫወትና በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ነፃ ሃሳባቸውን በተለያዩ የጽሑፍ ሥራዎቻቸው በማቅረብና ለኢትዮጵያ ህዝብ ይጠቅማል ብለው ያመኑበትን ሃሳብ በመንደፍ ይፋ በማድረግ ዝናቸው በሀገሪቱ ፖለቲካ ቁንጮ የፖለቲካ ንድፍ አውጭ በመሆን የሚታወቁት ዶ/ር ነገደ ጐበዜ የዚህ መጽሔት እንግዳ ሆነው ቀርበውልዎታል።**

**ዶ/ር ነገደ በወቅቱ የሀገራችን የምርጫ ሂደት ላይ ያላቸውን አይነተኛ ነጥቦች በማስቀመጥ ለኢህአዴግ ባለሥልጣናት ራስ ምታት ሆነው የሰነበቱ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ስላለው ፈጣን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በአንክሮ የተከታተሉትንና በጭንቀት የሚያሳልፉበትን እንዲሁም ያለፉ ትዝታቸውን ሁናቴ ጠይቀናቸዋል።**

**በዚህ ለህዝብ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡበትን ጊዜ ሰውተው እንግዳችን ለመሆን ፈቃዳቸው ስለሆነ ዶ/ር ነገደን ከልብ እናመሰግናለን።**

---

**ማለዳ፦** ምርጫው ተጭበርብሯል በሚል ተቃዋሚዎች ያቀረቡትን መሰረታዊ ክስ የማጣራት ሂደት እንደሚካሄድ ተወስኖ ነበር። ይሁንና ይህ የማጣራት ሂደት ከመጀመሪያውም ምርጫ በባሰ ሁኔታ የተበላሸና የተጭበረበረ ስለመሆኑ ሁለቱም ዋና ዋና ተቃዋሚ ፓርቲዎች የኮነኑት ከመሆኑም በላይ የዓለም አቀፍ ኮምዩኒቲም ይህንኑ ሃቅ የተገነዘበ ይመስላል። እስኪ በርስዎ በኩል የማጣራቱን ሂደት በተመለከተ ያሳደሩትን ግንዛቤ ያብራሩልኝ? በዚህስ አካሄድ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ምን መልክ ይዞ ይታይዎታል? በሀገሪቱ የተረጋጋና የሰከነ ሁኔታ ለመፍጠር ያሉት ወይም የቀሩት አማራጮች ምን መሆን አለባቸው ይላሉ?

**ዶ/ር ነገደ፦** 1997ን ምርጫ በተመለከተ ቀደም ብለን ያልነው (የዛሬ ዓመት ግድም)፣ የምርጫው ቦርድ ዋጋ የለውም፤ በኢህአዴግ ስር ምርጫ ዋጋ የለውም፤ ሁኔታዎች ይመቻቹ የሚል ክርክር እንደነበረ የሚታወስ ነው። እኛ ያልነው ምንድን ነበር፤ እንደኛ ሁኔታዎች ተሟሉ አልተሟሉ ብዙኀኑን ሕዝባችንን ይዘን የሚመጣውን ይዘን እንግባ። ብዙኀኑን ይዘን ከገባንና ሕዝባችን በገፍ ከተሳተፈ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት፣ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡም ፊት ተጋልጦ ነው "አሸነፍኩ" የሚለው። ይጋለጣል። ሲያጭበረብር ይያዛል የሚል ስትራተጂ ነበር የተከተልነው። እና አሁንም የሆነው ይኸው ነው። አሁን እንግዲህ ምርጫውን ከዳር እስከዳር አጭበርብሮታል። ይሄን ሁሉም ሰው የሚያውቀው ነው። ከዛ እንግዲህ እኛ እንዳለፈው ጊዜ ትግሉን ትተን አንበተንም፣ ተጨበርብሯል ብለን ትግሉን እንቀጥላለን የሚል አቋም ነበረን። እና ምርጫው ተጭበረበረ። ምርጫው ከተጭበረበረ በኋላ የማጣራት ሂደት ተብሎ ተቃዋሚዎችና ኢህአዴግ ተፈራረሙ። አሁን ስለሱ ነው ያነሳህብኝ ጥያቄ። ይሄንን እኔ መጀመሪያም ቢሆን ምንም ክፋት የለውም ነው ያልኩት - መፈራረማቸው። ምክንያቱም እንደገና ደግሞ ሲያጭበረብር ይያዛል የሚል አቋም ነበረኝ። እና የሆነው እንደዚሁ ነው።

ኢህአዴግ ድርብ ኪሣራ ነው የደረሰበት። አንደኛ ምርጫውን ሲያጭበረብር ተያዘ። በኛም ፊት፣ በኢትዮጵያ ህዝብም ፊት፣ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም ፊት። ሁለተኛ ደግሞ የማጣራቱንም ሂደት ሲያጭበረብር ተያዘ። አይደለም እንዴ?

> ”…አንዳንድ ሰዎች የሚሉት ‘ፓርላሜንቱ ውስጥ ገብተን ትግሉን እንቀጥላለን’ ይሄ በፍፁም የማይሆን ነገር አይደለም። …

የአውሮፓውያኖቹ ሪፖርት የሚለው 'የማጣራቱ ሂደት ተጭበርብሯል' ነው። እና እዚህ ላይ እንግዲህ የማጣራቱ ስምምነት በኢህአዴግና በምርጫ ቦርዱ መመሳጠር እና ከስምምነቱ ውጪ በተወሰዱ እርምጃዎች የማጣራቱ ሂደት ተኮላሽቷል። ከአሁን ወዲያ ፍርድ ቤት የሚለውም ነገር ዋጋ የለውም። ፍርድ ቤት የሚኬደው ከመጀመሪያው ነው። የዳኙነቱ ክፍል ነፃ ነው ሲባል ነው። ሁለተኛ ደግሞ ከሁሉም በላይ ፍርድ ቤት ከሄድህ በኋላ ያ ፍርድ ቤት የፈረደውን ፍርድ መቀበል ግዴታ ነው አይደለ? ካልተቀበልክ ሕገወጥ ነህ ማለት ነው። ስለዚህ ከአሁን ወዲያ እያወቅነው እጃችንን አንሰጥም። ፍርድ ቤት መሄድ አያስፈልግም። ሂደቱ ተቋርጧል። በኢህአዴግና በምርጫ ቦርዱ ሸፍጥ የተነሳ ፍርድ ቤት አንሄድም ብለን እዚያ ላይ ቆመናል ማለት ነው። እና ይሄ መፈረም አልነበረባቸውም መጀመሪያውኑም ምናምን የሚባለው ነገር እስከዚህም ዋጋ የለውም። አሁን የተሻለ ሁኔታ ላይ ነው ያለነው። ማለት ሁሉም ነገር ከዳር እስከዳር ተጭበርብሯል። ምርጫ ቦርዱም ከኢህአዴግ የሚመሳጠር መሆኑ ታውቋል። ስለዚህ አሁን በተሻለ ሁኔታ ላይ እንገኛለን - ትግሉን ለመቀጠል ማለት ነው።

**ማለዳ፦** ኢህአዴግ አሁን የያዘውን ለምባነናዊ አካሄድ አልቀይርም ብሎ ቢፀና የተቃዋሚዎች እርምጃ በተለይም በፓርላማው መሳተፍና አለመሳተፍን በተመለከተ ምን መሆን ይኖርበታል የሚለውን ጥያቄ ሕብረቱም ሆነ ቅንጅቱ ህዝቡን በስፋት ማነጋገር ይዟል። በግልዎ ይህንን ቁልፍ ጥያቄ አስመልክቶ ያለዎትን አስተያየት ብንጠይቅዎ ምላሽዎ ምንድን ነው? ተቃዋሚዎች ፓርላማ ገብተን ትግላችንን እንቀጥል ቢሉ ጥቅሙና ጉዳቱ ምን ይሆናል? በአንፃሩስ አንገባም ቢሉ የሚያስከትለው ችግርና የሚያስገኘውን ጠቀሜታ እርስዎ እንዴት ይመዝኑታል?

**ዶ/ር ነገደ፦** አሁን ያለንበት ሁኔታ ምርጫውን አጭበርብሮ አሸንፏል። እኛ ከመጀመሪያውም ያልነው (መጽሐፌን መጥቀስ ባይሆንብኝ) ምንድንነው - ያን ጊዜ ህዝቡ ነፃ ምርጫ የሚባል ነገር እንዳልተደረገና ድሉን እንደተቀማ አይቶ በቁጣ ይነሳል ነው መጽሐፌ ላይ የሚለው። በቁጣ ይነሳል፤ ያን ጊዜ ያንን ትግል መምራት ያስፈልጋል ነው። አሁን በትክክል የሆነው በእርግጥ ህዝቡ

> … ወይ ህዝባችን ያሸንፋል በሚመጡት በአንድ ወር በሁለት ወር በሚደረገው ትግል። ወይ ደግሞ ኅብረተሰቡ ተሸንፎ፣ ተንበርክኮ - በአመጽ የሚገዛበት። ሸብር ፈጣሪ መንግሥት የሚገዛበት ሁኔታ ይሆናል። በዛ ሂደት ፓርላሜንት ምን ሊሰራ እንደሚገባ አይገባኝም …



ቀስቃሽም አያስፈልገውም። ምክንያቱም ያለው ሁኔታ ህዝቡ ነው ተቃዋሚ ድርጅቶችን 'ግፋ እንጂ! በሉ እንጂ! ወደፊት በሉ! ...' እያለ የሚገፋፋው። እና በዚህ ጥያቄ ላይ እንግዲህ ምንድን ነው ይሄንን ውጤት ህዝቡ አልተቀበለውም። ይሄንን ውጤት ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አልተቀበለውም። እና ጉሚዝዝ የአውሮፓ ሕብረት ይሄንን ውጤት አይቀበለውም ብለዋል። ይሄንን ውጤት እኛ ተቃዋሚዎችም አንቀበለውም ብለናል። አይደለም እንዴ? እና ይሄንን ካልን በኋላ የሕብረቱም ውሳኔ የሚለው ቅንጅቶችም የሚሉት በማንኛውም ሠላማዊ የትግል ስልት፣ በሕጋዊ የትግል ስልት የህዝቡን ድል መልሰን እንጎናፀፋለን። ህዝቡ ድሉን እንዲጎናፀፍ እናደርጋለን የሚል አቋም አለን።

እንግዲህ በዚህ ላይ ቁርጠኛ ሆነን በዚህ ከፀናን የፓርላሜንቱ መግባት አለመግባቱ ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው። ለምንድን ነው እንደዚህ የሚሆነው፣ ትግሉ በሠላማዊ ሰልፍ፣ በሥራ ማቆም አድማ፣ ... በመሳሰሉት ነገሮች መቀጠል አለበት - ኢህአዴግ አልደራደረም ካለ። ምክንያቱም እኛ ቁርጥ ያለ አቋም ነው ያለን፣ አክራሪነት አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ ለኢህአዴግ አባላት መውጫ ቀዳዳ ሰጥተናል። ይሄውም ምንድን ነው፣ ከድሮም በፕሮግራማችን ያለ ነው የሽግግር መንግሥት የሚለው፣ እዚህ ሽግግር መንግሥት ውስጥ ኢህአዴግም ይወከልና ይገባል። በመሃል ዴሞክራታይዜሽን ታስኩች አሉ - የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን የሚባል አለ የሚቋቋም። እሱን እሱን አድርገን ኅብረተሰባችንን በሁለት ዓመት እንደዚህ ካመቻቸን በኋላ ወደ ነፃ ምርጫ እንሂድ የሚል ነው። አሁን ያለው ትግል የምርጫ ትግል ብቻ አይደለም። ምርጫው ይደገም፣ ሌላ ምርጫ ይካሄድ፣ ... ብቻ ምንም ይሁን ምን በዚህ ምርጫ ቦርድ ስር አይሆንም። መገናኛ ብዙኀኑ በኢህአዴግ ቁጥጥር ስር እንደሆነው አይሆንም። ሌሎች ሌሎች ዴሞክራቲክ ኮንሲሽንስ በሙሉ ከተሰጡ በኋላ ነው። ስለዚህ አሁን ያለንበት የትግል ምዕራፍ ለዴሞክራታይዜሽን መታገል ነው። እና ምንድን ነው የሚሆነው? ወይ ይሄ ትግል ይቀጥላል እና ያሸንፋል። ያን ጊዜ ፓርላማ ውስጥ መግባት ምንም ችግር አይኖረውም፣ አይደለም እንዴ? ወይ ደግሞ ይሄ ትግል ይሸነፋል። ኅብረተሰባችን መብቱን ለማስከበር፣ ድሉን ለማስከበር ተነስቶ ሲንቀሳቀስ፣ ኢህአዴግ በአመጽ ይሰማራና ይሄንን ትግል ያደናቅፈዋል። ኅብረተሰባችን ለጊዜውም ቢሆን ይሸነፋል። ያን ጊዜ አንገቱን የደፋ ኅብረተሰብ ነው የሚሆነው። እንደዚህ ሆኖ ሳለ፣ በሽፍጥ ከዚያ በኋላ ደግሞ በአመጽ በተቋቋመ ፓርላሜንት ውስጥ የተቃዋሚዎች መግባት ክህደት ነው የምለው። እና ይሄ በፍፁም መሆን የለበትም።

> ... እስከ ክፍለ ዘመኑ መጨረሻ ስንት መስዋዕትነት ተከፍሎ ስንት ሃሳቦች ተንሸራሽረው አሁንም እዛው ላይ ነን። ማለትም አሁንም ፍትሕ እንላለን፣ ዴሞክራሲ እንላለን፣ ሰላም እንላለን ...

ሌላ የሚነሳ ጥያቄ ደግሞ አለ። አንዳንድ ሰዎች የሚሉት 'ፓርላሜንቱ ውስጥ ገብተን ትግሉን እንቀጥላለን' ይሄ በፍፁም የሚሆን ነገር አይደለም። ህዝቡ መንገድ ወጥቶ ተሰውቶ፣ ታግሎ ያላስመለሰውን ድል፣ ፓርላሜንት ውስጥ ተገብቶ ይሄንን ትግል የሚተካ ከሆነ ማለቱ ነው። ይሄንን ህዝባችን ማካሄድ ያለበትን ሰላማዊ ትግል በሚተካ መልክ ፓርላሜንት ከተገባ ይሄም ራሱ ክህደት ነው ነው የምለው። እና ዞሮ ዞሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይፈታል ይሄ ነገር። ወይ ህዝባችን ያሸንፋል በሚመጡት በአንድ

ወር በሁለት ወር በሚደረገው ትግል። ወይ ደግሞ ኅብረተሰቡ ተሸንፎ፣ ተንበርክኮ - በአመጽ የሚገዛበት። ሽብር ፈጣሪ መንግሥት የሚገዛበት ሁኔታ ይሆናል። በዛ ሂደት ፓርላሜንት ምን ሊሰራ እንደሚገባ አይገባኝም። እኔ እንደዚህ ነው የማየው። ዋናው፣ ዋናው ጥያቄ በሚመጣው አንድ ወር፣ ሁለት ወር ትግሉ በተፋፋመና በሰከነ መልክ መቀጠሉ ነው። ያሸንፋል፣ ወይስ ይሸነፋል? ይሄ ሌላ ጥያቄ ነው። አሁን ግን ማተኮር ያለብን፣ ፓርላሜንት እንግባ አንግባ የሚለው ጥያቄ ላይ ሳይሆን፣ ይሄንን ትግል እንዴት እናፋፍመው ነው የምንለው። ይሄንን ትግል እንዴት የሰከነ እናድርገው ነው የምንለው።

ይሄንን ለማድረግ ደግሞ በሕብረቱ በኩል የቀረበ ፕሮፖዛል አለ። የኅብረተሰቡ ተወካዮች የኃይማኖት ስብሰቦች፣ የወጣቶች ተወካዮች፣ የሴቶች ተወካዮች፣ የገበሬዎች ተወካዮች፣ የአርበኞች ማኅበር፣ የንግድ ምክር ቤት፣ ... በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ ውስጥ አሉ የሚባሉ ኃይሎች ከያሉበት መጥተው፣ አንድ ሺህም አንድ ሺህ አምስት መቶም ሰዎች የሚገኙበት ሰፊ አገር አቀፍ ስብሰባ ተደርጎ ስትራቴጂ ያወጣል። በዚያ መሠረት ትግሉን እንቀጥላለን። ያንን ትግል ደግሞ ለመጀመር መስከረም ሃያና ሃያ አንድ ይሄ ስብሰባ ይደረጋል - አገር አቀፍ ጉባዔ። መስከረም ሃያ ሁለት በኢትዮጵያ ባሉ 22 - 23 ከተሞች ሰፊ የሆነ ህዝቡን በሙሉ ያካተተ ሠላማዊ ሰልፍ ይደረጋል። ኢህአዴግን "የህዝቡን ድምፅ አክብር! ለዚህም ደግሞ በተደረገው ጥሪ መሰረት ተደራደር!" የሚል ጥሪ ያቀርባል ማለት ነው። ይሄ ሳይሆን ግን አሁን ባለው ሁኔታ ሕብረቱ ጉባዔ ላይ ተብሏል፤ እንኳን ፓርላማ መግባት አለመግባት መወሰን ቀርቶ የህዝቡ ትግል በዚህ መልክ ሳይታጀብ ኅብረተሰቡ እንዳለ ተንቀሳቅሶ ሳይታጀብ፣ ካሁን ወዲያ ይላል ሕብረቱ፣ ችግሮቹን ለመፍታት በኢህአዴግና በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል በዓለም አቀፍ መሪዎች፣ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አጋፋሪነት የሚካሄድ ውይይት ፋይዳ የለውም' ነው የሚለው። ይሄ ዋጋ የለውም። አሁን ህዝቡ ትግሉ ውስጥ በሰከነ መልክ እንዲገባ የኅብረተሰቡ አሉ የሚባሉ መሪዎች በፈጠነ መልክ ይሄንን ትግል እንዲመሩ ማመቻቸት ነው ዋናው ጥያቄ። ለዚያም ደግሞ እየተሰራ ነው።

*__ማለዳ፦__ ከዚሁ ጋር የተያያዘ አንድ ጥያቄ እዚህ ጋር ላንሳ። ወደ ምርጫው ከመግባቱ በፊት ተቃዋሚዎች ይሉት የነበረው፣ እኛም አገር ቤት እያለሁ የማስታውሰው ምንድነው ነው፣ ይሄንን ትግል እስከመጨረሻው ድረስ የምንገፋው፣ ራሱ ኢህአዴግ ባዘጋጀው የምርጫ ሂደት ላይ ምርጫው የተጭበረበረና ትግሉ የከፋ መሆኑን ብናውቅም፣ እስከመጨረሻው በራሱ ሕግ እንታገለዋለን ብለው ነው ተቃዋሚዎች እዚህ ደረጃ ለመድረስ የቻሉት። የው በራሱ ሕግ ቢያጭበረብርም፣ ሌላም ችግር ቢፈጠር ይሄንን ነገር ታግለን ህዝቡንም እናታግላለን ብለው ነው። ይሄን ነገር ፓርላማ ከመግባት ጋር እንዴት ያዩታል? ይሄንን ነገር ከአሁን በፊት ከነበረው ጋር ምን ይለየዋልስ ይላሉ? ከአሁን በፊት የነበሩትስ የፓርላማ ሰዎች እዚህ ደረጃ ያደረሱትን ለውጥ አስመልክቶ ማለቴ ነው?*

__ዶ/ር ነገደ፦__ ጨርሶ የተለየ ሁኔታ ነው። ከዚህ በፊት 12ትም 15ትም ሰዎች

> *... አሁን ግን ማተኮር ያለብን፣ ፓርላሜንት እንግባ አንግባ የሚለው ጥያቄ ላይ ሳይሆን፤ ይሄንን ትግል እንዴት እናፋፍመው ነው የምንለው። ይሄንን ትግል እንዴት የሰከነ እናድርገው ነው የምንለው ...*

ፓርላመንት ገብተዋልና አሁን ደግሞ 200 ሁኖችኋልና የተሻለ ትሰራላችሁ የሚል አነጋገር አለ። ይህንን እኔ አውሮፓ ፓርላመንት ያደረኩት ንግግርም ላይ የዓለማቀፍ ኮሚኒቲውም እንደዚሁ ነበር የሚሉት። እና ባለፈው ቢሆን ምንም ችግር አልነበረም። አሁን ህዝባችን ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሷል፣ ከዳር እስከዳር ይህን ምርጫ ይህ መንግስት አጭበርብሮ ነው ያሸነፈው፣ ተሰውቼ፣ ታግዬ ያገኘሁትን ድል ተቀምቻለሁ የሚል በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ነው። ባለፈው ጊዜ እንደዚህ አልነበረም። ባለፈው ጊዜ ተጭበርብሯል የሚሉት ተቃዋሚ ድርጅቶች ብቻ ነበሩ። አሁን ግን ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄውን ብቻ ማንሳት አይደለም፣ ልሰዋ፣ ልታገል ካስፈለገ እያለ ግፊት እያደረገ ነው። ይህ አንድ ነገር ነው። ሁለተኛ ነገር ደግሞ ባለፉት ጊዜ ያልነበረ የውጭ ታዛቢዎች ሚና አለ። ዓለማቀፉ ማኅበረሰብ ልክ እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ ይህ ምርጫ ተጭበርብሯል እያለ ነው። ይህ ሁኔታ ባለበት ህዝባችን ታገሉና አታግሉኝ ባለበት ሁኔታ ፓርላማ ውስጥ ገብቶ እታገላለሁ ማለት፣ የህዝቡ ትግል ነው አሁን ዋናው ነገር እንጅ፤ የፓርላማ ትግል አይደለም። ምክንያቱም ህዝቡ ለመታገል ተነሳስቷል። እና ፓርላሜንት ውስጥ ገብቶ ትግል እካሂዳለሁ የሚባለው በተሸነፈ ሂደት ውስጥ ቅድም እንዳልኩት፣ መጀመሪያ ይህ ትግል መካሄድ አለበት። ወይ እናሸንፋለን ወይ ኅብረተሰባችን ይሸነፋል። ከተሸነፈም እዚህ ፓርላመንት ውስጥ ገብቶ ምን ፋይዳ እንደሚፈየድ በፍፁም አይገባኝም። ካሸነፈ ደግሞ ምርጫው የህዝቡን ድምፅ በሚያንጸባርቅ ሁኔታ ፓርላሜንት ውስጥ መግባት ነው። ግን ከመጀመሪያው ሕጉን አክብረን፣ በራሱ ሕግ ነው የምንጫወተው ስንል አሁንም ቢሆን ምርጫውንም ስንገባ የራሱን ሕግ እያከበርን ነው። እሱ ነው ሕጉን ማክበር ያቃተው። አሁንም ቢሆን ትግሉን የምንቀጥለው ሕጉን እያከበርን ነው። በኛ በኩል ምንም አይነት አመጽ አይኖርም። ባለፈው ሰልፍ 3 ሚሊዮን ህዝብ ወጥቶ አንድ ቅጠል አልተበጠሰም። አሁንም ቢሆን በዚህች ሀገራችን አመጽ የሚያስፈልገው ሕገ-ወጥ ነገር የሚያስፈልገው የኢህአዴግ መሪዎች እንጅ ተቃዋሚዎች ወይንም ህዝቡ አይደለም። አሁንም ቢሆን ሕጉን አክብረን ነው የምንሰራው። በሕገ-መንግስቱ ክልል ውስጥ ነው የምንሰራው። ሕገ - መንግስቱን እንቀይረዋለን ብለናል። የምንቀይረው ደግሞ በሕገ-ወጥ መንገድ አይደለም። በራሱ በሕገ-መንግስቱ ውስጥ ያሉትን አንቀጾች እየተጠቀምን ሕጋዊ በሆነ መልኩ ነው የምንቀይረው። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያሉት የማንስማማባቸው እስኪቀየሩ ድረስ ከሕጉ ሳንወጣ እንታገላለን። ይህ ደግሞ ከማሸነፍ አይመልሰንም ብየ ነው የምገምተው።

*__ማለዳ፦__ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሚና ምን ይሆናል ብለው ይጠብቃሉ? ይህ ምርጫ የተጭበረበረ ስለመሆኑ በተለይም የአውሮፓው ሕብረት አጥብቆ የከነነበት ሁኔታ ነው የታየው። ከዚህ አልፈው በአገዛዙ ላይ ምን ያህል ሚና እስከማሳደር ሊጓዙ ይጠበቅባቸዋል?*

__ዶ/ር ነገደ፦__ እንግዲህ እዚህ ጋር ምንድነው ... ወሎዎች የሚሉት ነገር አለ *"ይለያል ጉዱ፣ ይታያል ጉዱ"* የሚባል ነገር አለ - ሠርግ ላይ ሲዘፈን። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሰት ቆራጥና በዴሞክራሲያዊ ትግል ለሞት፣ ለመሰዋት፣ ለመታገል ዝግጁ የሆነ፣ የሌላው በሙሉ ግን ይታያል ጉዱ ነው። ተቃዋሚዎችም ይህንን ድል ለማስከበር ብቁ እንደሆንን እንታያለን። ዓለም አቀፉ ማኅበረሰቡም ይህ ምርጫ ተጭበርብሯል ካለ በኋላ፣ "በሉ ግድ የለም ለዚህ ግዜ እለፉት፣ ለሚቀጥለው አምስት ዓመት ተዘጋጁ" ማለት የራሳቸውን ማጠቃለያ እንኳን የማያከብሩ እንደሆኑ ይታያል። እየገፉን ያለነው

*(ወደ ፳፯ ዞሯል)*